የሰ/መ/ቁ. 49857

ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃነ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ፈትለወርቅ መንገሻ ፋንታ - ጠበቃ ገ/እግዚአብሔር ኪዳነ ቀረበ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ በላይነሽ ወ/ኪዳን - ወኪል ተሾመ አባይ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት እና የቦታ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ ተጠሪ ናት፡፡ ተጠሪ ክስ የመሰረተችው እማሆይ ፀሃይነሽ በተባለች ሰው እና በአሁንዋ አመልካች ላይ ሆኖ አመልካች ባለመቅረብዋ ክርክሩ በሌለችበት ተሰምቶ ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡ አከራካሪ ከነበሩት ጭብጦች አንዱ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በሚል በእማሆይ ፀሃይነሽ የተነሳው መቃወሚያ ስለሆነ የወረዳው ፍ/ቤት መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ በጉዳዩ ሥረ-ነገር ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ እማሆይ ፀሃይነሽ ውሳኔውን በመቃወም ይግባኝ አቅርባ ተቀባይነት እንዳላገኘ እና እስከ ሰበር ድረስም አቤቱታ አቅርባ ውድቅ እንደሆነባት በመዝገቡ ተመልክቶአል፡፡ ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ መዝገቡ(የወረዳው ፍ/ቤት) የተንቀሳቀሰው አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 78 መሰረት አቤቱታ በማቅረብዋ ነው፡፡ የወረዳው ፍ/ቤትም የአመልካችን ተቀብሎ ግራ ቀኝ ወገኖችን አከራክሮአል፡፡ በመቀጠልም የአመልካችና የይርጋ መቃወሚያ በመቀበል የቀድሞው ውሳኔውን ለውጦአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ በየደረጃው ለበላይ ፍ/ቤቶች ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ በማቅረብዋ ጉዳዩ እንደገና ታይቶአል፡፡ ጉዳዩን በመጨረሻ የሰማው የትግራይ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩ ቀደም ሲል ታይቶ በውሳኔ እልባት ያገኘ በመሆኑ አመልካች ያቀረበችው የይርጋ መቃወሚያ በድጋሚ የሚታይበት አግባብ የለም በማለት በወረዳው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ጥቅምት 17 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ በሥር የሰበር ችሎት በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የምትልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታዋን አቅርባለች፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው አመልካች ያቀረበችው የይርጋ መቃወሚያ ቀደም ሲል አንደኛ ተከሣሽ የነበረችው የአመልካች እናት አንስታው ውድቅ ሆኖአል በማለት ተቀባይነት ማጣቱ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ አመልካች እና ተጠሪ ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ከላይ እንዳመለከትነው አመልካች በዚህ ጉዳይ ተከራካሪ የሆነችው ተጠሪ ክስ ስላቀረበችበት ነው፡፡ በእርግጥ ክሱ በተሰማበት ጊዜ ልትቀርብ ባለመቻልዋ ጉዳዩ በሌለችበት ተሰምቶ ውሳኔ ተሰጥቶ እንደነበረ ግልጽ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 የተመለከተውን ድንጋጌ በመጠቀም ወደክርክሩ እንድትገባ ተፈቅዶላታል፡፡ በዚህ የሥነ-ሥርአት ሕግ ድንጋጌ እንደተመለከተው አቤቱታ አቅራቢው ወገን ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ የቀድሞው ውሳኔ ይነሳለታል፡፡ በዚህም ክርክሩ እንደና ይሰማል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ክርክሩ እንደገና ከተሰማ በኋላ የቀድሞው ውሳኔ ሊለወጥ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል ማለትም ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው አመልካች ለቀረበባት ክስ በሰጠችው መልስ ያዋጣኛል ያለችውን ክርክር አቅርባለች የተከሰሰችው በስምዋ እንደመሆኑ መጠን መከራከር የምትችለው(መከራከር ያለባት) እሷን (በግልዋ) የሚመለከት የመከራከሪያ ነጥብ በማንሳት ነው፡፡ የክርክር አቀራረብ ስልትዋም ሆነ የማስረጃ አቀራረብዋም እንደዚሁ በግልዋ ባቀረበችው ክርክር የሚወሰን ነው፡፡ ይህም ማለት ከስዋ ጋር ተከሳ የነበረችው ሰው ያነሳችው ክርክር የስዋም የመከራከሪያ ነጥብ እንደሆነ ተደርጐ የሚወሰድበት አግባብ የለም፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበችውን የይርጋ መቃወሚያ መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መታየት ያለበት ከዚህ አንፃር ነው፡፡ የሥር አንደኛ ተከሣሽ የነበረችው እማሆይ ፀሃይነሽ ያቀረበችውን የይርጋ መቃወሚያ መሰረት በማድረግ ከተሰጠው ውሳኔ ጋር የሚያያዝበት አግባብ የለም፡፡ ተደጋግሞ እንደተገለጸው አመልካች የክርክሩ ተካፋይ የሆነችው በግልዋ በቀረበባት ክስ ምክንያት በመሆኑ ክሱን መከላከል የምትችለው የግልዋ የመከራከሪያ ነጥብ እና የመከላከያ ማስረጃ በማቅረብ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳም ጉዳዩ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ ከተመለከተው ድንጋጌ አንፃር የሚታይ አይደለም፡፡ የሥር ሰበር ችሎት የአመልካች የይርጋ መቃወሚያ እማሆይ ፀሃይነሽ ባቀረበችው የይርጋ መቃወሚያ በተሰጠው ውሳኔ እልባት አግኝቶአል በማለት ያስቀመጠው ትችም ሆነ የደረሰበት መደምደሚያ ከሕጉ አተረጓጐም አንፃር ሲታይ መሰረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ የይርጋው መቃወሚያ በዚህ አግባብ ታይቶ ከመወሰኑ በፊት ወደ ጉዳዩ ሥረ-ነገር ገብቶ መወሰኑም ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ. 30402 መስከረም 29 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሮአል፡፡

2. የሰበር ችሎቱ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል አከራካሪ ሆኖ የቀረበው የይርጋ መቃወሚያ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖችን እንደገና ካከራከረ በኋላ ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡

3. ግራ ቀኝ ወገኖች በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ